# በመሚያ ቁጥር 01/2001 ስለ ግል ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ የተደነገጉትን ለማሻሻል የወጣ መሚያ ቁጥር 059/2013

አዲስ አበባ ከተማ

አስተዳደር ጤና ቢሮ

2007 ዓ/ም

# በመመሪያ ቁጥር 01/2001 ስለ ግል ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ የተደነገጉትን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 059/2013

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ

2007 ዓ/ም

# ማውጫ

**መግቢያ** ..... **1**

**ክፍል አንድ** ..... **2**

**ጠቅላላ ድንጋጌ** ..... **2**

አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ ..... 2
አንቀጽ 2. ትርጓሜ ..... 2
አንቀጽ 3. አወጪው ባለስልጣን ..... 2
አንቀጽ 4. የመሜሪያዉ ተፈጻሚት ወሰን ..... 2
አንቀጽ 5. የመሜሪያዉ አላሞዎች ..... 3

**ክፍል ሁለት** ..... **4**

**የግል ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ሞርሆዎች** ..... **4**

አንቀፅ 6. የግል ህክምና አግልግሎት አሰጣጥ ሞርሆዎች ..... 4

**ክፍል ሦስት** ..... **5**

**የግል ህክምና አገልግሎት ስለማቋቋም፡ አደረጃጀት እና አስተዳደር** ..... **5**

አንቀጽ 7. የግል ህክምና አገልግሎት ስለማቋቋም ..... 5
*7.1 ስለግል ህክምና አገልግሎት የማቋቋሚያ ውሳኔ ..... 5*
*7.2 ስለግል ህክምና አገልግሎት ምስረታ ጊዜያዊ ኮሚቴ ..... 5*
*7.3 መነሻ የሀብት ምንጭ ..... 6*
*7.4 የአገልግሎት ቅንጀት እና ስብጥር ..... 6*
አንቀጽ 8. የግል ህክምና አገልግሎት አደረጃጀት ..... 6
አንቀጽ 9. የግል ህክምና አገልግሎት ማስጫ ክፍል አስተዳደር ..... 7
*9.1 በግል ህክምና አገልግሎት የሰራተኞች አመዳደብ ..... 7*
*9.2 የግል ህክምና አገልግሎት የሥራ ሰዓት ..... 8*

**ክፍል አራት** ..... **9**

**መብትና ግዴታ** ..... **9**

አንቀጽ 10 የተገልጋዮች መብትና ግዴታ ..... 9
*10.1 የተገልጋዮች መብት ..... 9*
*10.2 የተገልጋዮች ግዴታ ..... 9*
አንቀጽ 11. የተቋሙ ግዴታዎች ..... 9

**ክፍል አምስት** ..... **10**

**ስለ የዋጋ ተመን፣ የገቢ ክፍፍል፣ የፋይናንስ አስተዳደር እና ኦዲት** ..... **10**

አንቀጽ 12. የግል ህክምና ክፍል አገልግሎት የዋጋ ተመን ..... 10
አንቀጽ 13. የገቢ ክፍፍል ..... 10
አንቀጽ 14. የፋይናንስ አስተዳደር ..... 11
*14.1 የገቢ አሰባሰብና ክፍያ አፈጻጸም ..... 11*
*14.2 የግል ህክምና መስጫ ክፍል የገቢ ምንጮች ..... 12*
*14.3 የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ..... 12*
*14.4 የኦዲት አገልግሎት ..... 12*
*14.5 የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ..... 13*

ክፍል ስድስት ....14

ተግባር፣ ኃላፊነት እና ክትትልና ግምገማ ....14

አንቀጽ 15. የጠቅ ቦሮ ተግባርና ኃላፊነት ....14
አንቀጽ 16. የሆስፒታሉ የሥራ አመራር ቦርድ ....14
አንቀጽ 17. የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/ፕሮቮስት ....15
አንቀጽ 18. የግል ህክምና ክፍል ኃላፊ ....16
አንቀጽ 19. ክትትልና ግምገማ ....17

ክፍል ሰባት ....18

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ....18

አንቀጽ 20. ተጠያቂነት ....18
አንቀጽ 21. መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ ....18
አንቀጽ 22. የተሻሩ መመሪያዎች ....18
አንቀጽ 23. ተፈጻሚነት ....18

ANNEXS ....20

COST OF PROVIDING SERVICES AND PROCEDURES IN PRIVATE WING AT HOSPITAL LEVEL ....20

1. LABORATORY ....20
2. MINOR SURGERY ....21
3. NURSING CARE & PROCEDURES ....22
4. MAJOR SURGERIES ....22
5. OPHTHALMOLOGY PROCEDURES ....25
6. DENTAL PROCEDURES ....26
7. RADIOLOGY TEST ....27
8. ENT ....29
9. MISCELLANEOUS ....29

# መግቢያ

በሆስፒታሎች የሚሰጠውን የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃውን የጠበቀና በሥርዓት የሚመራ እንዲሆን ለማስቻል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ አስተዳደርና አመራር የተሻሻለዉ አዋጅ 08/2001 በከተማ አስተዳደሩ ምክር ቤት ማጽደቁ ይታወቃል፡፡ ይህንኑ አዋጅ ይበልጥ ለማብራራትና ተፈጻሚ ለማድረግ እንዲረዳ በማሰብ የከተማ አስተዳደሩ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ አስተዳደርና አመራር ደንብ 26/2001 በካቢኔ ወጥቷል፡፡ መመሪያ ቁጥር 1/2001 እንዲሁም ልዩ ልዩ የአፈጻጸም ማኑዋሎች በከተማ አስተዳደሩ ጤና ቢሮ ማውጣቱ ይታወሳል በዚህም የህግ ማዕቀፍ ወስጥ በመንግሥት ሆስፒታሎች የግል ህክምና ክፍል አገልግሎት አሰራርና አደረጃጀት ሰፍሮ ይገኛል፡፡

የዚህ አገልግሎት መጀመር የባለሙያዎችን የስራ ተነሳሽነት በመጨመርና ባሉበት ሆስፒታል ረጅም ጊዜ ቆይተው እንዲያገለግሉ ከማስቻሉም በላይ ለህብረተሰቡ አማራጭ የህክምና አገልግሎት ሆኗል፡፡ ይሁን እንጂ በአሠራሩ ላይ በተደረጉ ጥናቶች የአላቂ እቃዎች ለሆስፒታሉ የሚመለስበት ስርአት አለመኖር፣ የግል ህክምና አገልግሎት በመደበኛ የህክምና አገልግሎት ሰዓት ማስራት፣ የሰው ሃይል አመዳደብ መርሆ አለመኖር፣ የአገልግሎት ዋጋ ወጥ ያለመሆን፣ የገቢ ትርፍ ክፍፍል ስርአት አለመኖር እና የመሳሰሉት ችግሮች የተስተዋሉ በመሆኑና ከተጠቃሚው ህብረተሰብ በሚነሱ ጥያቄዎች መሠረት ከዚህ በፊት በወጣው መመሪያ ላይ ያልተሸፈኑ ሁኔታዎችን ለማብራራትና የዋጋ ትመና ጣሪያ ለማስቀመጥ መመሪያውን ማሻሻል በማስፈለጉ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ወይይት ከተደረገበት በኋላ  በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ይህ የማሻሻያ  መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «በመመሪያ ቁጥር 01/2001 ስለ ግል ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ የተደነገጉትን ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 059/2013» ተብሎ ሊጠራ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፣

1. **"የግል ህክምና አገልግሎት"** ከድንገተኛ ሕክምና አገልግሎት ወጪ ከመደበኛ የህክምና አገልግሎት ጎን ለጎን ባለሙያዎች ከስራ ሰዓት ወጪ በበዓላት ቀን በተመጣኝ ክፍያ የተሟላሽና የተሻቶ ሕክምና አገልግሎት ለማስጠት የተቋቋመ አገልግሎት ማለት ነው፡
2. **"የመደበኛ የሕክምና አገልግሎት ክፍል"** ማለት ሆስፒታሉ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ለመደበኛ ሕክምና አገልግሎት ተገቢው የጤና ክብካቤ የሚሰጥበት ክፍል ነው፡
3. **"ሜጅመንት"** ማለት የሆስፒታሉ ሜጅመንት ማለት ነው፡
4. **"የግል ህክምና አገልግሎት ማስረታ ጊዜያዊ ኮሚቴ"** ማለት ከተለያዩ የሆስፒታሉ ክፍሎች ከተወጣጡ ባለሙያዎች የሚዋሰረትና የግል ህክምና መስጫ ክፍሉን በሆስፒታሉ ወስጥ ለማቋቋም አዋጭነቱን በዝርዝር አጥንቶ የውሣኔ ሃሣብ የሚያቀርብ ቡድን ነው፡
5. **«ድንገተኛ ህክምና»** ***ማለት የወሊድ አገልግሎትን*** በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ምክንያት በስተቀር ***ቅጽበታዊ እርዳታ የሚያሻው ያልተጠበቀና የከፋ የጤና መታወክ ሲያጋጥም የሚደረግ የህክምና አገልግሎት ነው::***
6. **"የአገልግሎት ጥራት"** ማለት የተገልጋዩን ህብረተሰብ የጤና አገልግሎት ፍላጎትና የተቀመጡ ስታንዳርዶች በተሟላ ደረጃ ተግባረዊ በማድረግ የሚፈለገውን ወጤት ማምጣት ማለት ነው፡
7. **"ሆስፒታል"** ማለት ተጠሪነቱ ለከተማ አስተዳደሩ ጤና ቢሮ የሆነ የጤና አገልግሎት መስጫ የጤና ሞያ ማስተሚሪያ የመንግስት ጤና ተቋም ነው፡
8. በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴት ፆታም ያገለግላል፡፡

### አንቀጽ 3. አወጪው ባለስልጣን

ይህንን መመሪያ ያወጣው ባለስልጣን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ነው፡

### አንቀጽ 4. የመመሪያዉ ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተጠሪነታቸው ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ለሆኑ የመንግስት **ሆስፒታሎች ላ□** ተፈጻሚ **ይሆናል::**

## አንቀጽ 5. የመመሪያዉ አላማዎች

**ይህ መመሪያ የሚከተሉትን አላማዎች ለማሳካት ያለመ ነዉ፡፡**

5.1 **የጤና ባለሙያዎች በትርፍ ጊዜያቸው ለሚሰጡት አገልግሎት ተጨማሪ ቆጢ እ□ዮኙ፤ በጤና ተቋሙ ውስጥ እንዲቆዩ በማበረታታት፣ የስራ ተነሳሽነታቸውን ማሳደግና የሙያተኞችን ፍልሰት መቀነስ፡፡**

5.2 **የመክፈል አቅም ያላቸውን ተገልጋዮች በምርጫቸው የሚፈልጉትን የህክምና ባለሙያና የአገልግሎት አይነት በሚፈልጉት ሆስፒታል በሚመቻቸው ቀንና** የግል ህክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ሰዓት **እንዲያገኙ በማድረግ ተገልጋዮች በሚያገኙት አገልግሎት እንዲረኩ ማስቻል፡፡**

5.3 **ከግል ህክምና አገልግሎት በሚገኘው ተጨማሪ ገቢ በመጠቀም የመደበኛ አገልግሎትን ማሻሻል፡፡**

## ክፍል ሁለት
## የግል ህክምና አገልግሎት አሰጣጥ መርሆዎች

### አንቀፅ 6. የግል ህክምና አግልግሎት አሰጣጥ መርሆዎች

ሀ. የግል ህክምና አገልግሎት የሚሰጠው □መ□በኛውን አገልግሎት በማያስተጓጉልና በሚያጠናክር መልኩ መሆን አለበት::

ለ. ከምግብ፤ ከመኝታ □አሎች አገልግሎትና አገልግሎቱን ለማግኘት ከሚፈጀው ቲ□ በስተቀር በመ□በኛውና በግል ህክምና አገልግሎት መካከል የአገልግሎት ጥራት ልዩነት መኖር የለበትም::

ሐ. የግል ህክምና አገልግሎቱ መቋቋም በመ□በኛ የህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍሎች የሚሰጠውን □ቀ□ሮ ቲዜ ለማሳጠር የሚደረገውን ጥረት ማወክ የለበትም፡፡

መ. በመ□በኛው የህክምና አገልግሎት ያልተጀመሩ ወይንም የማይሰጡ የህክምና አገልግሎቶች በፅል ህክምና ክፍሉ መጀመር ወይም መስጠት የለባቸውም፡፡

ሠ. □መ□በኛ የህክምና አገልግሎትን ለመጠቀም የመጣን ወይም ህክምና እየተከታተለ ያለን ታካሚ በማንኛውም መልኩ የግል ህክምና አገልግሎትን እንዲጠቀም ተፅዕኖ ማድረግ የተከለከለ ነው::

ረ. በግል ህክምና አገልግሎት ህክምናውን እየተከታተለ ያለ ታካሚ ወደ መደበኛ ህክምና በበቂ ምክንያት (የገንዘብ አቅም፣ የጤና ሁኔታ፣ የህክምና ውስብስብነት፣ ወዘተ) ማዛወር ቢያስፈልግ የግል ህክምና አገልግሎት ኃላፊና የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር በመነጋገር ሊፈጸም ይችላል፡፡

ሰ. በግል ህክምና አገልግሎት ስራ ላይ ያለ ባለሙያ ለድንገተኛ ህክምና አገልግሎት ሲ□ለፅ ያለክፍያ የመስራት ግዴታ አለበት::

ሸ. □ግል ህክምና አገልግሎት የህክምና የቡድን አሰራር መንፈስን በተከተለ መልኩ የሚሰራ መሆን ይኖርበታል::

ቀ. የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት በግል ህክምና አገልግሎት □አል መስጠት የተከለከለ ነው::

## ክፍል ሦስት

## የግል ህክምና አገልግሎት ስለማቋቋም፣ አደረጃጀት እና አስተዳደር

### አንቀጽ 7. የግል ህክምና አገልግሎት ስለማቋቋም

#### 7.1 ስለግል ህክምና አገልግሎት የማቋቋሚያ ውሳኔ

የግል የሕክምና መስጫ ክፍል ሊቋቋም የሚችለው በዚህ መመሪያ የተካተቱ ነጥቦችን መሰረት በማድረግ የማቋቋሚያ ሀሳብ ሲቀርብ በሆስፒታሉ ማኔጅመንት በሚሰየም የግል ህክምና አገልግሎት ምስረታ የቴክኒክ ጊዜያዊ ኮሚቴ በሚካሄድ ጥናትና የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/ፕሮቮስት በሚያቀርበው የውሳኔ ሃሳብ መሰረት በሆስፒታሉ ቦርድ ተገምግሞ ሲጸድቅ ይሆናል፡፡

#### 7.2 ስለግል ህክምና አገልግሎት ምስረታ ጊዜያዊ ኮሚቴ

የግል ህክምና መስጫ አገልግሎትን በሆስፒታሉ ወስጥ የማቋቋም አዋጭነት በዝርዝር አጥንቶ የውሳኔ ሃሣብ የሚቀርብ ኮሜቴ ነው፡፡ ይህም ኮሜቴ በሆስፒታሉ ሜጅመንት ይሰየማል፡፡ **የግል ህክምና** አግልግሎት ምስረታ **ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡፡**

**ሀ. የሆስፒታሉን ነባራዊ ሁኔታ በመገምገም የግል ህክምና አገልግሎት አዋጭነትን ያጠናል፡፡**

**ለ. በግል ህክምና ክፍል ሊሰጡ የሚችሉ የጤና አገልግሎቶችን ይለያል፡፡**

**ሐ. የግል ህክምናውን ተግባር እና አላማ ለማሳካት የሚረዳ የገበያ ጥናት ያካሂዳል፡፡**

**መ. የሰው ኃይል ጥናት፣ የአሰራር ጥናትና የፋይናንስ ጥናት በማድረግ በወቅቱ የተለዩ ስጋቶችንና ታሳቢዎችን በዝርዝር ይለያል፡፡**

**ሠ. በግል ህክምና ክፍል የሚሰጡ አገልግሎቶችን ዝርዝር ያዘጋጃል፡፡**

**ረ. ከላይ ከፊደል ሀ-ሠ የተገለጸው ጉዳዮችን የያዘ ሰነዶችን አጠናክሮ ለሆስፒታሉ ማኔጅመንት ያቀርባል፡፡**

**ሰ. የግል ህክምና አገልግሎት ምስረታ** ጊዜያዊ **ኮሚቴ የግል ህክምና አገልግሎቱ ሲጀመር የስራ ጊዜው ያበቃል፡፡**

## 7.3 መነሻ የሀብት ምንጭ

7.1.1 የግል ህክምና ማስጫ አገልግሎት ማቋቋሚ ካፒታል የሆስፒታሉ የስራ አመራር ቦርድ በሚፈቅደው መሰረት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በአንዱ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ምንጭ በተገኘ ካፒታል ሊቋቋም ይችላል፡፡

1. ከሆስፒታሉ መደበኛ የዉስጥ ገቢ ከሚገኝ ከወለድ ነጻ ብድር፣
2. ከመንግሥት ከሚገኝ የበጀት ድጋፍ እና
3. እንዳስፈላጊነቱ ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ገቢ ሊቋቋም ይችላል::

የግል ህክምና አገልግሎት ማቋቋሚያ ካፒታል ከሆስፒታሉ የዉስጥ ገቢ ወይም ከመንግሥት ከሚገኝ የበጀት ድጋፍ በብድር የተገኘ ከሆነ የብድሩ መመለሻ ጊዜ በሆስፒታሉ የስራ አመራር ቦርድ ይወሰናል::

### 7.3.2 ስለ ቋሚ ንብረት

ለግል ህክምና አገልግሎት የተቋሙን ቋሚ ንብረት □ለ□አ□ መ□ቀም ይቻላል:: ሆኖም ግን የመደበኛውን አገልግሎት የማያስተጓጎል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው::

### 7.3.3 ስለ አላቂ ንብረቶች

ሀ/ የግል ህክምና □አሉ አገልግሎቱን ለመጀመር ሲወሰን የራሱ አላቂ ንብረቶች እንዲኖሩት □□ረፉል፤

ለ/ የግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍሉ አላቂ ንብረቶችን በራሱ ማዘጋጀት ካልቻለ በተቋሙ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ ነገር ግን በግዥ ዕቅድ መካተቱንና በ□ወሩ የተጠቀመውን ቁሳቁስ ሂሳብ ለተቋሙ ቱኪ እንዲያደርግ የሚያስችል □አሠራር ማዘርጋትና ተፈፃሚነቱም በውስጥ ኦዲት እንዲህም ማኔፀመንቱ ማረጋገጥ ይኖርበታል::

## 7.4 የአገልግሎት ቅንጅት እና ስብጥር

7.4.1. □ፅል ህክምና አገልግሎቱ በሆስፒታሉ እንዲጠቀምበት □ተ□ቀ□ለትን መሰረተ-ልማት እና የህክምና መሳሪያዎች ያለምንም ወቸ መ□ቀም □ችላል፤ ሆኖም ፅን □ተሽከርካሪ አገልግሎት ወቸ በክፍያ ይሆናል::

7.4.2 የስራ ተያያዥነት ያላቸው የመደበኛ አገልግሎት ልዩ ልዩ ክፍሎች ከግል ህክምና አገልግሎት ጋር ተቀናጅተው መስራት አለባቸው::

## አንቀጽ 8. የግል ህክምና አገልግሎት አደረጃጀት

ሀ. የጤና ተቋማት የግል ህክምና አገልግሎት በተመላላሽ ወ□ም/እና በተኝቶ ህክምና አገልግሎት ሊደራጅ ይችላል::

ለ. የግል ህክምና የተኝቶ ህክምና አገልግሎት ከመደበኛው የተኝቶ ህክምና አገልግሎት የተለየ ክፍል ያለው ሆኖ ከመደበኛው አጠቃላይ አገልግሎት አልጋ ከ10% የበለጠ መጠቀም አይችልም፡፡

ሐ. ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አጠቃልይ ለግል ህክምና አገልግሎት ከተመደበው አልጋ ወስጥ በመደበኛ አገልግሎት ባሉት ክፍሎች የሥራ ጫና አንፃር ይከፋፈላል፡፡

መ. የግል ህክምና አገልግሎት የራሱ የሙሉ ጊዜ ኃላፊ እና ጸሐፊ/ ሪሴፕሽኒስት ይኖረዋል፤ የሰራተኞቹ የደመወዝ አከፋፈል በማግስት የሲቪል ሰርቪስ መሜሪያ ማስረት ሆኖ ተጨማሪ እንደ አገልግሎቱ ማበን የማትግያ ክፍያ በቦረዱ ወሰኔ ይከፈላቸዋል፡፡ የግል ህክምና ክፍሉ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/ፕሮቮስት ሆኖ የሜጅመንት ኮሜቴ አባል ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 9. የግል ህክምና አገልግሎት ማጫ ክፍል አስተዳደር

### 7.5 በግል ህክምና አገልግሎት የሰራተኞች አመዳደብ

**የሆስፒታሉ ማኔጅመንት፡-**

ሀ. በመደበኛ አገልግሎት አሰጣጥ በእውቀታቸው፣ በችሎታቸው፣ በተነሳሽነታቸው፣ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ባላቸው የሥራ ውጤትና በሙያ ስነ-ምግባራቸው የተሻሉ እና ፍቃደኝነታቸው እየታየ በግል ህክምና ክፍል ውስጥ በሚወጣው የሥራ ፕሮግራም መሰረት በየተራ እየተመደቡ እንዲሰሩ ያደርጋል፡፡

ለ. አንድ ባለሙያ በግል ህክምና አገልግሎት ሰዓት የሚሰጠው አገልግሎት በምጣኔ ሲሰላ በመደበኛ አገልግሎት ከሰጠው ግልጋሎት አንጻር አጠቃላይ በግል ህክምና አገልግሎት ያከናወናቸው ተግባራት ምዘና የመደበኛውን አገልግሎት ስልሳ በመቶ (60%) መብለጥ የለበትም፡፡ ይህንንም ለማስፈፀም እንድያስችል የእያንዳንዱ ፈፃሚ ባለሙያ የግል የዕለት ሥራ አፈፃፀም መከታተያ መዝገብ (Log Book) በሆስፒታሉ ይዘጋጅለታል፡፡

ሐ. በመደበኛ ህክምና ለተኝቶ ህክምና አገልግሎት የሚመደብ የሰው ኃይል መጠን በምጣኔ ለግል ህክምና አገልግሎት የተኝቶ ታካሚዎች መመደብ ይኖርበታል፡፡

መ. ማንኛውም በግል ህክምና አገልግሎት ለመሳተፍ የሚፈልግ ባለሙያ የኮንትራት ውል ከሆስፒታሉ ጋር መፈራረም ይኖርበታል፡፡

ሠ. በተመሳሳይ ሰዓት በመደበኛ ወይም በተረኝነት ተመድቦ የሚሰራ ባለሙያ በግል ህክምና አገልግሎት መመደብ የለበትም፡፡

ረ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ኃላፊ በውድድር/በምደባ የሚመደብ ሲሆን በኃላፊነት የሚመደበው የጤና ባለሙያ ወይም ከጤና ጋር ተያያዥነት ያለው ሌላ ሙያ ያለዉ ሆኖ፣ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪና የአራት አመት የሥራ ልምድ ሊኖረዉ ይገባል፡፡

ሰ. ተጨማሪ የግል ህክምና አገልግሎቶች ባለሙያ በኮንትራት በመቅጠር መመደብ ቢያስፈልግ የግል ህክምና ክፍል ግልጽ የማወዳደሪያ መስፈርት ማውጣት ይኖርበታል፡፡

ሸ. ለግል ህክምና ክፍል አገልግሎት የጥበቃ፣ የጽዳት፣ ጠቅላላ አገልግሎት፣ የሰው ሃብት አስተዳደር፣ የውስጥ ኦዲት፣ ፋይናንስ፣ ግዥ፣ ስምሪት እና የመጋዘን የመሳሰሉት አገልግሎቶችን ሲጠቀሙ የሆስፒታሉን መደበኛ አገልግሎትን በማያስተጓጉል መልኩ መሆን አለበት፡፡

ቀ. በግል ህክምና ክፍል ውስጥ የድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ምደባ ከላይ በዚሁ ንኡስ አንቀፅ 1/ሀ/ በተጠቀሰው መሰረት በዙርና በየተራ እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡

በ. የግል ህክምና አገልግሎት ለሚያከናውናቸው ሥራዎች በመደበኛው አገልግሎት የሚሰሩ ሰራተኞች አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

## 7.6 የግል ህክምና አገልግሎት የሥራ ሰዓት

በግል ህክምና መስጫ ክፍል የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት የሥራ ሰዓት፡-

**1. ለተመላላሽ ታካሚዎች የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት ሰዓት**

ሀ. ዘወትር ከሰኞ እስከ አርብ ከሥራ ሰዓት ውጭ ከ11፡30 እስከ ምሽቱ 4፡00 ይሆናል፤፤

ለ. ዘወትር ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በሕዝባዊ በዓላት ወቅት ከጠዋቱ 2፡00 እስከ ምሽቱ 12፡00 ሰዓት ይሆናል፤፤

ሐ. በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በወረፋ ብዛት አልያም የሚከናወነው ፕሮሲጀር ረዘም ያለ ጊዜ የሚጠይቅ ከሆነ የተጠቀሰው የሥራ ሰዓት በእለቱ ብቻ ሊራዘም ይችላል፤፤

**2. ለተኝቶ ታካሚዎች የሚሰጥ የህክምና አገልግሎት**

ሀ. የነርሲንግና የሐኪም ክትትል አገልግሎት በግል ህክምና ክፍል በተመደቡ ሰራተኞች ብቻ ለ24 ሰዓት የሚሰጥ ይሆናል፤፤

ለ. የቀዶ ጥገና አገልግሎት ሊሰጥ የሚችለው ከላይ በንኡስ አንቀፅ

1/ሀ/ እና /ለ/ በተጠቀሰው ሰዓት ብቻ መሆን አለበት፤፤

## ክፍል አራት

## መብትና ግዴታ

### አንቀጽ 10 የተገልጋዮች መብትና ግዴታ

### 7.7 የተገልጋዮች መብት

**አጠቃላይ የሆስፒታል ተገልጋይ መብቶች እንደተጠበቁ ሆኖ**

ሀ. በተቻለ አቅም አጭርና የተመቻቸ የህክምና ቀ□ሮ ማፅኘት

ለ. ተቆልፋ□ በ□ለቱዉ ባለሙ□ □መታከም

ሐ. ተገልጋዩ ከአሎ ካርድ ካወጣበት ቀን ጀምሮ ለተመሳሳይ የህክምና ችግር ለተከታታ□ 7 ቀናት □ለተ□ ማሪ □ክርት □አ□ □ህክምና አገልግሎቱን ማፅኘት

መ. በግል ህክምና አገልግሎት የሚሰጠውን የአገልግሎት □ር□ር፣ዋጋ እና የባለሞዎች የሞ ደረጃ ፣ የስራ ልምድና ብቃት የማወቅ

ሠ. ለታከመው ህክምና በፅሁፍ የሀከም ማስረጃ የማግኘት መብት ይኖራቸዋል፤፤

### 7.8 የተገልጋዮች ግዴታ

ሀ. □መ□በኛዉና የግል ህክምና አገልግሎቱን ህግና ደንብ ማክበር፣

ለ. የህክምና ስነ-ምግባርን ከሚጋፉ ድርጊቶች መቆጠብ፣

ሐ. ለግል ህክምና አገልግሎት የተተመነውን ቅድሚያ ክፍያ መፈፀምና አገልግሎቱን ሲጨርስ ሂሳቡን ማወራረድ፣

### አንቀጽ 11. የተቋሙ ግዴታዎች

ሀ. በግል ህክምና የሚሰጠው አገልግሎት በመደበኛውም አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን ማሳወቅ፣

ለ. የተሻለ የአገልግሎት አቅርቦት እንደ ምግብ፤ አልጋና ሌሎች አገልግሎቶች □ማቅረብ፣

ሐ. በመ□በኛውም ሆነ በግል ህክምናው የሚሰጠው አገልግሎት በጥራቱ ተመሳሳይ መሆኑን ማሳወቅ፣

መ. ሁሉንም አይነት የአገልግሎት ዋጋ ተመን ግልጽ በሆነ ቦታ መለ□አ፣ማሳወቅ

ሠ. ሐኪሞች ሙሉ ስማቸውን፤ የሙያ አይነትና አገልግሎት የሚሰጡበትን ቀን በግልፅ መለ□አ፤

ረ. አገልግሎቱ በሆስ□ታሉ በመ□በኛዉ አገልፅሎት እስካልተሰ□ ትረስ በግል ህክምና ክፍሉ እንዳይሰጥ ማድረግ፤

ሰ. በግል ህክምናው አገልፅሎት ተመድበው በመስራት ላይ □ሉ □ሆስ□ታሉ ሰራተኞች በተለ□□ ምክንያቶች ስራ ሲ□ስተጓቶሉ □መ□በኛውን ስራ እንደበ□ሉ ተቆጣጥሮ አስ□ላጊዉን □እርምት እርምጽ መዉሰት፤

ቀ. አገልግሎቱ በ□ህ መመሪ□ በተፈቀደው ሰዓት ብቻ መሰጠቱን ማረጋገጥ፣

## ክፍል አምስት

## ስለ የዋጋ ተመን፣ የገቢ ክፍፍል፣ የፋይናንስ አስተዳደር እና ኦዲት

### አንቀጽ 12. የግል ህክምና ክፍል አገልግሎት የዋጋ ተመን

በግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል ታካሚው ለተሰጠው አገልግሎት የሚከፍለው የክፍያ ታሪፍ በታካሚው ላይ ከፍተኛ ጫና በማይፈጥርና ለባለሙያዎች ተመጣጣኝ ገቢ በሚያስገኝ አግባብ ሆኖ በጤና ቢሮው ከተዘጋጀው የአገልግሎት ክፍያ ጣሪያ ሳይበልጥ በቦርድ እየፀደቀ ተግባራዊ ይሆናል፡፡ (ዝርዝሩ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ሆኗል)

### አንቀጽ 13. የገቢ ክፍፍል

ከሆስፒታሉ የግል ህክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል ጠቅላላ ገቢ ላይ የአላቂ መገልገያ ወጪዎች ከተቀነሱ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ ከአገልግሎቱ የተገኘ ትርፍ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ከተጣራው የግል ህክምና ገቢ 70% ለጤና ባለሙያ 15% ለሆስፒታል እና ቀሪው 15% ለአስተዳደርና ለድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ይውላል፡፡ ከሁሉም እኩል 1 አንድ በመቶ ተቀንሶ 3% የግል ህክምና ክፍል ቀጣይነትን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

ሀ. የባለሙያዎቹ ድርሻ የሆነው 69% የትምህርት ደረጃ፣ የአገልግሎት ዘመን፣ በሥራው ላይ ያለው ተፈላጊነትና ያሳለፈውን የሥራ ሰዓት ባገናዘበ መልኩ እንደ ሆስፒታሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ በሚወጣ የግል ህክምና አገልግሎት የገቢ ክፍፍል ቀመር መሰረት በቦርድ በማፀደቅ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

ለ. ለአስተዳደርና የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ድርሻ ከሆነው 14% ውስጥ የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/ፕሮቮስት ብር እስከ 3000 ፣ ሜዲካል ዳይሬክተር/ም.ፕሮቮስት/ ም. ሥራ አስኪያጅ ብር እስከ 2500 እና የግል ህክምና አገልግሎት ኃላፊው ብር እስከ 4000 የማትግያ ክፍያ እንደ ሆስፒታሉ የገቢ መጠን ይከፈላቸዋል፤፤ እንዲሁም የአስተዳደር ሰራተኞች ክፍያ በቁርጥ የሚወሰን ሆኖ ቀሪው ለድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በቀመር ይከፋፈላል፡፡

ሐ. የክፍያ መጠን እና የአከፋፈል ቀመር የሥራ አመራር ቦርድ ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የተደረገውን ስሌት መነሻ በማድረግ እንደ ሆስፒታሉ ሁኔታ የሚወሰን ይሆናል፡፡

መ. በግል ህክምና አገልግሎት ስም ተቀናሽ ተደርጎ የሚቀመጠው 3% ገቢ የግል ህክምና አገልግሎቱን ዘላቂነት ለሚያረጋግጥ የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/ፕሮቮስት ገንዘቡን ለመጠቀም እቅድ ሲያቀርብና የሥራ አመራር ቦርዱ ሲያፀድቀው ገንዘቡ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፣

ሠ. ከግል ህክምና አገልግሎት የሚገኘው 14% የሆስፒታሉ ድርሻ የተቋሙ የውስጥ ገቢ አካል ሆኖ ሁለንተናዊ የሆስፒታሉን አገልግሎት ጥራት ለሚያሻሽሉ ተግባራት የሚውል ይሆናል።

ረ. ከላቦራቶሪ እና ዲያግኖስቲክስ አገልግሎት የሚገኝ ትርፍ የላቦራቶሪና የዲያግኖስቲክስ ባለሙያዎች ድርሻ ከተቀነሰ በኋላ ወደ ፑል ገብቶ የሚከፋፈል ሲሆን ማንኛውም ሀኪም ካዘዘው የላቦራቶሪ ወይም የዲያግኖስቲክስ ምርመራ አገልግሎት ክፍያ በቀጥታ ገቢ ሊያገኝ አይገባም፡፡

ሰ. በአንቀጽ 13 ሀ እና ለ የተጠቀሰው የገቢ ክፍፍል ጣሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ የግል ህክምና ክፍሉ ገቢ ዝቅተኛ ሆኖ ሲገኝ የስራ አመራር ቦርድ በሚወስነው መጠን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 14.   የፋይናንስ አስተዳደር

### 7.9 የገቢ አሰባሰብና ክፍያ አፈጻጸም

ሀ. ለግል ህክምና መስጫ ክፍል የሚፈጸሙ ክፍያዎች፣ግዥዎችና የንብረት አስተዳደር ሥራዎች የመንግስት የፋይናንስ መመርያን የተከተሉ መሆን አለባቸዉ፡፡

ለ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል የሚሰበስበዉ ገቢ በሆስፒታሉ የግል ህክምና አገልግሎት ስም በከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ምዝገባና ፈቃድ በሚታተም ደረሰኝ ይሆናል፡፡

ሐ. የሚሰበሰበዉ ገቢ ለግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት እንዲዉል በሚከፈት ልዩ የባንክ ሂሳብ በየዕለቱ ገቢ ይደረጋል፡

መ. ገቢዉ ለዚሁ አገልግሎት በሚመደቡ የዕለት ገቢ ሰብሳቢዎች አማካኝነት የሚሰበሰብ ሲሆን ፣ በሚቀጥለው ቀን ወደ ባንክ ገቢ መሆን ይኖርበታል፣  እስከዚያው ድረስ በአስተማማኝ ካዝና እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

ሠ. የባንክ ሂሳብ ማንቀሳቀስ የሚቻለው በሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/ፕሮቮስት፣ በሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተርና በሆስፒታሉ ሂሳብ ክፍል ኃላፊ ሆኖ፣-

1. በሆስፒታሉ ሂሳብ ክፍል ኃላፊና በሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/ፕሮቮስት ጣምራ ፊርማ ወይም
2. የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/ፕሮቮስት በሌለ ጊዜ በሆስፒታሉ ሂሳብ ክፍል ኃላፊ እና የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ይሆናል፡፡

### 7.10 የግል ህክምና መስጫ ክፍል የገቢ ምንጮች

ሀ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል የገቢ ምንጮች ሆስፒታሉ የሚሰጣቸዉ

- የተመላላሽና የተኝቶ ህክምና አገልገሎት፤
- የላቦራቶሪና የዲያግኖስቲክስ አገልግሎቶች
- የምግብ እና የመኝታ አገልግሎት
- የጤና ምርመራ ማስረጃ (medical certificate) አገልግሎት እና
- ሌሎች በግል ህክምና የሚሰጡ ተጓዳኝ የህክምና አገልግሎቶች ይሆናሉ፡፡

ለ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ገቢ ከመድኃኒትና ከአላቂ የህክምና መገልገያ እቃዎች ሽያጭ የሚገኘን ገቢ አያጠቃልልም፡፡

ሐ. ሆስፒታሉ ለሚሰጣቸዉ የግል ህክምና አገልግሎቶች የሚገኘዉ ገቢ ለክፍያ አፈጻጸምና በግልጽ ለሚቀርብ የፋይናስ ሪፖርት አጋዥ ይሆን ዘንድ ለየገቢ ምንጩ የመንግስት የፋይናንስ ኮድ እንዲኖረዉ ይደረጋል

መ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል ከሶስተኛ ወገን ጋር በሚደረስ ስምምነት መሰረት የዱቤ አገልግሎት መስጠት ይችላል፡፡

### 7.11 የሂሳብ መዝገብ አያያዝ

ሀ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል የራሱ የሆነ የሂሳብ መዝገብ፤ የባንክ ሂሳብ፤ የገቢ ደረሰኝና ልዩ ልዩ ቅጻቅጾች ከመደበኛዉ ሂሳብ ተለይተዉ ይኖሩታል፡፡

ለ. ማንኛዉም የግል ህክምና መስጫ ክፍል ገቢና ወጪ በየዕለቱ በሂሳብ መዝገብ መመዝገብና በጥንቃቄ መያዝ አለበት፡፡

ሐ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል የሚጠቀምባቸዉ የሂሳብ ሰነድ ዓይነቶች ይዘት በመደበኛዉ አገልግሎት ሥራ ላይ የሚዉሉት አይነት ይሆናሉ፡፡

መ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል በዱቤ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሂሳብ መዝገብ በአግባቡ ተመዝግቦ በጥንቃቄ መያዝ ይኖርበታል፡፡

ሠ. የግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት የሂሳብ አያያዝ የከተማ አስተዳደሩን የሂሳብ አያያዝ አዋጅ፡ ደንብና መመሪያ ተከትሎ ይፈጸማል፡፡

### 7.12 የኦዲት አገልግሎት

ሀ. የሆስፒታሉ የዉስጥ ኦዲተር ስለየግል ህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎትና የሂሳብ አያያዝ ለሆስፒታሉ ሥራአስኪያጅ/ፐሮቮስት ክትትል በማድረግ ያማክራል፤ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

**ለ.** **የግል ህክምና መስጫ ክፍል ሂሳብ በየወሩ በዉስጥ ኦዲተር ይመረመራል፡፡**

**ሐ.** **የግል ህክምና መስጫ ክፍል ሂሳብ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ በዉጭ ኦዲተር** እንዲሚሚር ይደረጋል፡፡

**መ.** **የግል ህክምና መስጫ ክፍል ሂሳብ የሚመረመረዉ በከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡**

## 7.13 የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ

14.5.1 የግል ህክምና ማስጫ ክፍል አገልግሎት ሂሳብ በሂሳብ ክፍሉ ተዘጋጅቶ በየወሩ፣ በሩብ አመት እና በዓመት ለግል ህክምና ክፍል ኃላፊ ይቀርባል፡፡ የግል ህክምና ክፍል ኃላፊ የቀረበለትን የሂሳብ ሪፖርት ገምግሞ ለሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/**ፕሮቮስት**ና ለሌሎች ለሚሞለከታቸዉ አካላት በወቅቱ ማቅረብ አለበት፡፡ 14.5.2 የግል ህክምና ማስጫ ክፍል አገልግሎት የ**ከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ** በሚያሳትማቸው የሂሳብ ማቅረቢያ ፎርሞችን በማጠቀም፡

1. የገቢ ሪፖርት
2. የወጪ ሪፖርት
3. የተሰብሳቢ ሪፖርት
4. የተከፋይ ሪፖርት
5. የሂሳብ ሚዛን
6. ሳጥን ሂሳብ ሪፖርት
7. የባንክ ማስታረቂያ ርፖርት መቅረብ አለበት፡፡

14.5.3. የግል ህክምና ማስጫ ክፍል አገልግሎት አጠቃላይ አመታዊ ሪፖርት ለሆስፒታሉ ሜጅመንትና ለቦርዱ ቀርቦ ማምገምና መጽደቅ ይኖርበታል፡፡

**14.5.4.** የግል ህክምና ማስጫ ክፍል በየወሩ የትርፍና ኪሳራ ማገለጫ ከሪፖርት ጋር አካቶ ማቅረብ አለበት፡፡

# ክፍል ስድስት

## ተግባር፣ ኃላፊነት እና ክትትልና ግምገማ

### አንቀጽ 15. የጠፍ ቦሮ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ. የግል ሕክምና አገልግሎት አሰራርን አስመልክቶ ጥናት ያካሄዳል፣ የአሰራር ማሻሻያ ያደርጋል፡፡

ለ. የግል ሕክምና አገልግሎት አሰራርን አስመልክቶ መልካም ተሞክሮችን ይቀምራል፣ ያሰፋል፡፡

ሐ. ለግል ሕክምና አገልግሎት ማጠናከሪያ የሚሆን ሁለንተናዊ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

መ. የግል ሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ መከታተያና መገምገሚያ መስፈርት ያወጣል አሰራሩን ለማጠናከር የሚያስችል የድጋፋዊ ክትትል ስርዓት ይዘረጋል፡፡

ሠ. ስለግል ሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ የሚቀርብለትን የአፈፃፀም ሪፖርቶች ይገመግማል ግብረ መልስም ይሰጣል አስፈላጊውን የእርምት እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

### አንቀጽ 16. የሆስፒታሉ የሥራ አመራር ቦርድ

ሀ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ለማቋቋም በቀረበው ሰነድ ላይ ተወያይቶ ክፍሉ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡

ለ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ተግባር በበላይነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

ሐ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን በተመለከተ የሚከናወኑ የማስተዋወቅ ሥራዎችን በበላይነት ይደግፋል፡፡

መ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ኃላፊ ምደባ በሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/ፐሮቮስት በሚቀርብለት የውሳኔ ሃሳብ መሰረት ይወስናል፡፡

ሠ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ለማቋቋም የሚያስፈልገውን የመነሻ ካፒታል መጠንና ምንጭ ይወስናል፡፡

ረ. በዚህ መመሪያ የወጣውን የክፍያ ማዕቀፍ መሰረት አድርጎ የግል ሕክምና መስጫ ክፍል የአገልግሎት ክፍያ ተመን ያጸድቃል፤ መፈጸሙን ይከታተላል፡፡

ሰ. የግል ህክምና አገልግሎትን የገቢ ክፍፍል ቀመር ያጸድቃል፤ ይከታተላል፡፡

ሸ የግል ሕክምና አገልግሎት አስተዋፅኦና የአገልግሎት አሰጣጡ የሚሻሻልበትን ሁኔታ ይገመግማል፣ ይከታተላል፡፡

ቀ. የግል ሕክምና ክፍሉን አስመልክቶ የቀረበውን የወር፣ የሩብ ዓመት፣ የግማሽ አመትና አመታዊ ሪፖርቶችን ይገመግማል ግብረ መልስም ይሰጣል አስፈላጊውን የእርምት እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

በ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን አመታዊ እቅድና በጀት ገምግሞ ያፀድቃል፡፡

ተ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ኦዲት እንዲደረግ አመራር ይሰጣል ሪፖርቱንም ይገመግማል፡፡

## አንቀጽ 17. የሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/ፕሮቮስት

ሀ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ለመቋቋም የሚያስችል ጊዜያዊ የቴክኒክ ኮሚቴ ከማኔጅመንቱ ጋር በመሆን ይመርጣል ይሰይማል፡፡

ለ. በጊዜያዊ የቴክኒክ ኮሚቴ ተጠንቶ የቀረበውን ጥናት ገምግሞ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ለሆስፒታሉ የሥራ አመራር ቦርድ አቅርቦ ያስወስናል፡፡

ሐ. የወጣውን መስፈርት መነሻ በማድረግ ማኔጅመንቱን ባሳተፈ ሁኔታ የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉን ኃላፊ በመምረጥ ለሥራ አመራር ቦርዱ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

መ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ ያለውን ሥራ ለማከናወን የሚያግዙ ጊዚያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፡፡

ሠ. የግል ህክምና መስጫ ክፍሉን ለማስጀመር፣ ለማጠናከርና ለማስፋፋት የሚያስፈልገውን ሀብት ያፈላልጋል፡፡

ረ. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ የሚከናወነውን ተግባር ለመከታተል የሚያስችል ቼክሊስት ያዘጋጃል፣ በዚሁ መሰረት ክትትል ያደርጋል የማሻሻያና የእርምት እርምጃ ይወስዳል፡፡

ሰ. የግል ሕክምና አገልግሎት ከመደበኛ አገልግሎት ጋር የተቀናጀ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ሸ. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ በየወቅቱ የሚቀርብለትን ሪፖርት ገምግሞ ለሆስፒታሉ የሥራ አመራር ቦርድ ያቀርባል፡፡

ቀ. የግል ህክምና አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ የማስተዋወቅ ተግባራትን ያስተባብራል፡፡

በ. በግል ህክምና መስጫ ክፍል ውስጥ ስለሚሰጠው የአገልግሎት ጥራትና በክፍሉ ውስጥ የተመደቡት ሰራተኞች የህሙማን አቀባበል በተመለከተ ከደንበኞች ግብረ መልስ ይቀበላል፣ ይገመግማል፣ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

ተ. የግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ኦዲት እንዲደረግ አመራር ይሰጣል ሪፖርቱንም ይገመግማል፤ ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

ቸ. በሆስፒታሉ ሥራ አመራር ቦርድ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 18. የግል ህክምና ክፍል ኃላፊ

ሀ. በግል ህክምና አገልግሎት ውስጥ የሚከናወኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን ይከታተላል፣ አግባብ ያለው የሂሳብ አያያዝና አመዘጋገብ ተግባር መፈፀሙን ያረጋግጣል፤ በሂሳብ ባለሙያዎች ተዘጋጅቶ የቀረበውን የሂሳብ መግለጫ ገምግሞ ለሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/ፕሮቮስት ያቀርባል፡፡

ለ. የአገልግሎት ጥራትና በክፍሉ ውስጥ የተመደቡት ሰራተኞች የህሙማን አቀባበልን በተመለከተ ከደንበኞች ግብረ መልስ ይቀበላል፣ ይገመግማል፣ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

ሐ. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲደረጉ የተተመኑ ወይም የተከለሱ የአገልግሎት ክፍያዎች በአግባቡ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፣

መ. በየጊዜው ክትትል በማድረግ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የሚያስችሉ አሠራሮችን ተግባራዊ በማደረግ ሙስና፣ ብክነትና ምዝበራ እንዳይፈጠር ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

ሠ. በግል የሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኞችን መርሃ ግብር ያዘጋጃል፣ ሰራተኞችን ይመድባል፣ የተመደቡ ሰራተኞችን ዝርዝር በግልፅ ቦታ በመለጠፍ ሰራተኞች እንዲያውቁት ያደርጋል፣ ሰራተኞች በምድብ ቦታቸው ተገኝተው መሥራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በወሩ መጨረሻም አስፈላጊውን መረጃ ለሂሳብ ክፍል ያስታውቃል፡፡

ረ. በግል የህክምና መስጫ ክፍል ከሚሰጡ አገልግሎቶች የሚሰበሰቡ ገቢዎችና የሚፈፀሙ ክፍያዎች፣ የመንግትን የገቢ ግብር በደንብና መመሪያ መሠረት መከናወናቸውን በመከታተል ያረጋግጣል ለማኔጅመንት ኮሚቴና ለሥራ አመራር ቦርዱ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡

ሰ. መደበኛና ድንገተኛ ኦዲት በባለሙያዎች በማካሄድ የግል ህክምና አገልግሎት አሰጣጡ የታለመውን አላማ ያሳካ ስለመሆኑ ይገመገማል፡፡

ሸ. በግል የህክምና መስጫ ክፍል አገልግሎት የሚሠጡ የቴክኒክና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች የሥራ ውል እንዲፈራረሙ በማድረግ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

ቀ. በግል ሕክምና ክፍሉ ውስጥ ስለሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ ለተገልጋዩ ሕብረተሰብ የማስተዋወቅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

በ. በግል ሕክምና ክፍሉ ውስጥ የሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት በመደበኛ የህክምና ክፍሉ ከሚሰጠው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፣ ተመሳሳይነቱንም ይከታተላል፣ ልዩነት ሲፈጠር የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል እንዲወሰድም ያደርጋል፡፡

ተ. ለግል ሕክምና ክፍሉ የሚያስፈልጉ ግብኣቶችን በመለየት ለሚመለከተው ክፍል ጥያቄ ያቀርባል፣ የተጠየቁት ግብአቶች ተሟልተው መቅረባቸውን ይከታተላል፡፡

ቸ. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ አዳዲስ የሕክምና አገልግሎቶችን ለማስጀመር ጥያቄ ሲቀርብ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሚመለከታቸውን ክፍሎች በማማከር አዳዲስ አገልግሎቶች እንዲጀመሩ የውሳኔ ሀሳብ ለሥራ አስኪያጁ/ፕሮቮስት ያቀርባል፡፡

ነ. በግል ሕክምና መስጫ ክፍሉ ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትን በተመለከተ ወርሃዊ የሩብ ዓመትና አመታዊ ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/ፕሮቮስት ያቀርባል፡፡

ኘ. በየሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ/ፕሮቮስት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 19. ክትትልና ግምገማ

የግል ህክምና አገልግሎት አሠራር እና ጥራት ላይ ጥብቅ ክትትል እና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡ በክትትል እና ግምገማ ሥራወም የጠፍ ቢሮ፤ የሆስፒታል ቦርድ፤ የግል ህክምና ክፍል፤ የሆስፒታል ሜጅመንት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሰራሉ፡፡

ለዚህ ግምገማ እና ክትትል የሚያስፈልጉ የመረጃ ምንጮች በሆስፒታሉ ከሚገኝ መረጃና በHMIS ከሚጠናቀር ሪፖርት ይሆናል፡፡ ክትትልና ግምገማ በተዘጋጀ ቼክሊስት እና በተመረጡ አመላካቾች (Indicators) የወር፣ የሩብ አመት፣ የግማሽ አመት እና የአመት ሪፖርት በየደረጃው ለሚመለከታቸው አካላት ይቀርባል፡፡ በተዋረደም ሪፖርትቱን በመገምገም ግብረ መልስ ይሰጣል ድጋፋዊ ክትትልም በየጊዜው የሚደረግ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 20. ተጠያቂነት

20.1 ማንኛውም የግል ህክምና የሚሰጥ የከተማ አስተዳደሩ ሆስፒታል ይህንን መመሪያ ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

20.2 በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን የአሰራር ስርዓቶችን ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሆስፒታል እንደ ጥፋቱ ሁኔታና ክብደት እየታየ የግል ህክምና አገልግሎቱን ማዘጋት ጨምሮ አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰዳል፡፡

20.3 ማንኛውም በግል ህክምና ክፍል ተመድቦ የሚሰራ ሰራተኛ እና የሥራ ኃላፊ በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን የአሰራር ስርዓት የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡

20.4 በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን የአሰራር ስርዓቶችን ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰራተኛ እና የሥራ ኃላፊ እንደጥፋቱ ሁኔታና ክብደት እየታየ ከግል ህክምና ክፍሉ ከማሳገድ ጀምሮ በማንግስት የሲቪል ሰርቪስ ህግና በፍታብሄር እንዲሁም በወንጀል ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 21. መመሪያው ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

የጤና ቢሮው ይህንን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘበት ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

### አንቀጽ 22. የተሻሩ መመሪያዎች

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና አገልግሎት አሰጣጥ፣ የጤና ተቋማት አስተዳደርና አመራር መመር□** ቁጥር 1/**2001** ክፍል 7 ከአንቀጽ 76 እስከ 86 ያሉት ተሽረው በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡

### አንቀጽ 23. ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ ከነሐሴ 01/2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ/2007 ዓ.ም

ግርማ አሸናፊ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጤና ቢሮ ኃላፊ

**አመልካቾች (Indicators)**

የሚከተሉት አመልካቾች የዚህን ፕሮግራም ውጤታማነት ለማምገም ለመከታተል ይውላሉ፡፡

| ተ.ቁ | አመልካቾች (Indicators) | ሪፖርት የማድረጊያ ጊዜ |
|---|---|---|
| 1 | የመደበኛ ተመላላሽ ታካሚዎች ቁጥር ከግል ህክምና ተመላላሽ ታካሚዎች ቁጥር በንፅፅር፣ | በየወሩ |
| 2 | የመደበኛ የተኝቶ ታካሚ ቁጥር ከግል ህክምና የተኝቶ ታካሚ ቁጥር በንፅፅር፣ | በየወሩ |
| 3 | ከሆስፒታሉ ምን ያህሉ አልጋ ለግል ህክምና አገልግሎት ተመድቧል | በየሩብ አመቱ |
| 4 | በሆስፒታሉ ካሉ ስፔሻሊስት ሐኪሞች ምን ያህሉ በግል ህክምና አገልግሎት ይሳተፋሉ፣ | በየሩብ አመቱ |
| 5 | የስፔሻሊስቶች Attrition Rate: ከሆስፒታሉ የሚለቁ የስፔሻሊስት ሐኪሞች ብዛት መጀመሪያ ከነበረው የስፔሻሊስት ሐኪሞች ቁጥር ተካፍሎ በመቶኛ ይሰላል፣ | በየስድስት ወሩ |
| 6 | በመደበኛ የሥራ ቀናት አንድ የቀዶ ሕክምና ባለሙያ በግል ህክምና አገልግሎት ሰዓት የሰጠው አገልግሎት እና መደበኛ አገልግሎት ሰዓት ከሰጠው አገልግሎት በምጣኔ፣ | በየወሩ |
| 7 | ሆስፒታሉ ካገኘው ጠቅላላ ገቢ ወስጥ ምን ያህሉ የግል ህክምና አገልግሎት ድርሻ ነው፣ | በየሩብ አመቱ |
| 8 | የመደበኛ ተኝቶ ታካሚ የቆይታ ጊዜ በአማካይ ከግል ህክምና ተኝቶ ታካሚ የቆይታ ጊዜ በንፅፅር፣ | በየወሩ |
| 9 | በግል ሕክምና አገልግሎት ተሳታፊ የሆኑ ሰራተኞች እርካታ፣ | በየስድስት ወሩ |
| 10 | በግል ሕክምና አገልግሎት ከተጠቀሙ ህሙማን የአገልግሎት እርካታ፣ | በየስድስት ወሩ |

## Annexs

## Cost of Providing Services and Procedures in Private Wing at Hospital Level

### 1. Laboratory

**ማስሰቢያ፡ -** ተገልጋዩ በቀጥታ ከሚከፍላው የግል ህክምና አገልግሎት ክፍያ (PW price) ላይ በተጨማሪ የአላቂ እቃዎች ዋጋ (PW supply cost) ተቀንሶ ለሆስፒታሉ ገቢ ከተደረገ በኋላ ቀሪው በግል ህክምና አገልግሎት የተገኘ ትርፍ ይሆናል፡፡ የአላቂ እቃዎች ዋጋ ከስር ከተመለከተው የሚጨምር ከሆነ በሆስፒታል ሜጅመንት እየታየ ለስተካከል ይችላል፡፡

| No. | Services | PW Price | Estimated supply cost |
|---|---|---|---|
| 1. | AFB | 15 | 7 |
| 2. | ASO titer (serial) | 124 | 40 |
| 3. | B/F | 10 | 3 |
| 4. | Blood Group | 20 | 13 |
| 5. | Body fluid analysis (peritoneal, synovial, plural, etc | 40 | 18 |
| 6. | CBC | 30 | 7 |
| 7. | Cervical mucus analysis | 12 | 3 |
| 8. | Cholesterol | 30 | 10 |
| 9. | CSF analysis | 40 | 13 |
| 10. | ESR | 13 | 5 |
| 11. | FBS/RBS | 10 | 5 |
| 12. | Fungs scraping/koh/ | 15 | 8 |
| 13. | Gram stain | 40 | 12 |
| 14. | H. pylory stool | 100 | 47 |
| 15. | H. Pylory AB | 50 | 27 |
| 16. | HBSAg | 30 | 13 |
| 17. | HCT | 10 | 4 |
| 18. | HCV | 40 | 19 |
| 19. | HGB | 7 | 2 |
| 20. | L.F.T (Got ,GPT,ALP) | 40 | 12 |
| 21. | Pregnancy Test | 15 | 5 |
| 22. | R. F.T (urea & creatinine) | 38 | 13 |
| 23. | RBC morphology/peripheral blood morphology | 15 | 7 |
| 24. | Rheumatoid Factor (RF) | 19 | 9 |
| 25. | RPR | 17 | 9 |

| No. | Services | PW Price | Estimated supply cost |
|---|---|---|---|
| 26. | Skin snip | 24 | 9 |
| 27. | Sperm analysis | 39 | 18 |
| 28. | Stool Direct | 10 | 2 |
| 29. | Triglycerides | 15 | 6 |
| 30. | U/analysis Test | 17 | 10 |
| 31. | Uric Acid | 18 | 6 |
| 32. | VDRL | 17 | 9 |
| 33. | WBC | 10 | 5 |
| 34. | Weil flix | 14 | 7 |
| 35. | Wet Smear | 20 | 10 |
| 36. | Widal | 31 | 10 |
| 37. | Electrolytes and lipid profile | 118 | 30 |
| 38. | Hormonal assay | 120 | 40 |

## 2. Minor Surgery

| | | |
|---|---|---|
| 1. | Abscess drainage | 51 |
| 2. | Anal dilation (large) | 339 |
| 3. | Anal Dilation (simple) | 176 |
| 4. | Bouginage | 89 |
| 5. | Breast Lump removal | 336 |
| 6. | Cauterization | 384 |
| 7. | Chest tube insertion | 244 |
| 8. | Chest tube removal | 40 |
| 9. | Circumcision | 133 |
| 10. | Cystostomy | 250 |
| 11. | Dressing surgical wound | 60 |
| 12. | Fibro adenoma excision | 341 |
| 13. | Gastric lavage | 54 |
| 14. | Hydrocelectomy | 518 |
| 15. | Ingrowth toe-nail excision | 349 |
| 16. | Intra-articular injection | 181 |
| 17. | Lipoma/ganglion/dermoidcyst excision( big ) | 344 |
| 18. | Long arm Cast | 174 |

| | | |
|---|---|---|
| 19. | Long leg cast | 239 |
| 20. | Lumbar puncture | 95 |
| 21. | Lymph node biopsy | 134 |
| 22. | Paracenthesis/therapeutic | 88 |
| 23. | Pericardiosynthesis | 160 |
| 24. | Peritoneal fluid taping | 23 |
| 25. | Rectal Tube deflation | 240 |
| 26. | Removal of cyst/lipoma(simple) | 245 |
| 27. | Removal of Foreign Body from Ear and Nose | 214 |
| 28. | Short leg cast | 141 |
| 29. | Simple & incisional biopsy | 329 |
| 30. | Supply of Oxygen inhalation/hr | 10 |
| 31. | Thoracentesis(diagnostics) | 55 |
| 32. | Thoracentesis (therapeutic) | 91 |
| 33. | Urethral or bladder irrigation | 19 |

## 3. Nursing Care & Procedures

| | | |
|---|---|---|
| 1. | Nursing care for non-bedridden patients per day | 60 |
| 2. | Nursing care for post-surgery per day | 80 |
| 3. | Nursing care for bedridden patient per day | 80 |
| 4. | Nursing care for comatose patient per day | 100 |
| 5. | Application of Cast | 47 |
| 6. | Colostomy Irrigation (Care) | 20 |
| 7. | Ear Irrigation | 19 |
| 8. | Enema | 25 |
| 9. | NGT Insertion | 13 |
| 10. | Perennial Care | 10 |
| 11. | Post Mortem Care | 100 |
| 12. | Removal of Cast | 15 |
| 13. | Stich Removal | 10 |

## 4. Major Surgeries

| | | |
|---|---|---|
| 1. | Abdomino-perineal resection of bowel | 2,688 |
| 2. | Barthelin's abscess | 500 |
| 3. | Big mass excision with GA | 2,605 |
| 4. | Bone marrow aspiration with GA | 900 |

| | | |
|---|---|---|
| 5. | Cerclage | 752 |
| 6. | Thoracic Surgery | 2,988 |
| 7. | Cholecystectomy (Complicated) | 3,090 |
| 8. | Cholecystectomy (Simple) | 2,704 |
| 9. | Clitoral cyst. big with anesthesia | 1,680 |
| 10. | Club foot correction | 1800 |
| 11. | Colostomy Cloture (Complicated) | 3,170 |
| 12. | Colostomy Cloture (Simple) | 2,588 |
| 13. | Complicated fracture with debridement | 2,100 |
| 14. | Cystolithomy(stone removal from urinary bladder) | 2,373 |
| 15. | Depressed skull fracture Burr hole elevation | 2,556 |
| 16. | Dislocation/Closed reduction | 1,792 |
| 17. | Dislocation/open correction (Elective) | 2,619 |
| 18. | D and C | 742 |
| 19. | Elective Caesarian Section | 1,637 |
| 20. | Finger Amputation | 1,432 |
| 21. | Fistuloctomy expect obstetric | 2,342 |
| 22. | Gasterojejinoostomy with vagotomy | 2,736 |
| 23. | Goo-Vagotomy | 2300 |
| 24. | Hemorrhoidectomy | 2,257 |
| 25. | Hernorrhaphy with general anstesia | 2,007 |
| 26. | Hernorrhaphy with local Anstesia | 1,338 |
| 27. | Imperforated anus (Specify cut back) | 2,302 |
| 28. | Imperforated anus (Simple) | 1800 |
| 29. | Imperforated hymen | 654 |
| 30. | Laparotomy | 2,636 |
| 31. | Lower Limb Amputation | 2,271 |
| 32. | Mastectomy (Radical) | 2,958 |
| 33. | Mastectomy (Simple) | 2,588 |
| 34. | MVA(Manual Vacuum Aspiration) | 504 |
| 35. | Myomectomy | 1,830 |
| 36. | Nephrectomy | 2,967 |
| 37. | Nephrolithotomy anduretero-lithotomy | 2,568 |
| 38. | Other gastro intestinal major surgery | 2,740 |
| 39. | Other major urologic surgeries | 2,807 |

| | | |
|---|---|---|
| 40. | Other Major orthopedics surgery | 3,500 |
| 41. | Other major neurosurgical procedures | 3,950 |
| 42. | Ovarian cyst. Removal big | 2,470 |
| 43. | Ovarian cyst. Removal small | 1,664 |
| 44. | Prostatectomy simple | 2,443 |
| 45. | Prostatectomy complicated | 2,968 |
| 46. | Redundant sigmoid volvulus resection & anastomosis | 2,662 |
| 47. | Repair of Ligaments and other plastic surgery | 2,680 |
| 48. | Repair of Tendons | 2,691 |
| 49. | Sequestrectomy (General) | 2,548 |
| 50. | Sequestrectomy /local/ | 1,700 |
| 51. | Thyroidectomy (Sub-total) | 2,534 |
| 52. | Thyroidectomy (Total) | 2,896 |
| 53. | Varicose vein milking and ligation | 2,300 |

## 5. Ophthalmology Procedures

| | | |
|---|---|---|
| 1. | Capsulotomy /squint | 622 |
| 2. | Chelazion/curettage | 897 |
| 3. | Conjunctiva tear | 1,192 |
| 4. | Corneal tear | 1,581 |
| 5. | Correction of intropion | 1,117 |
| 6. | Dressing for corneal ulcer | 670 |
| 7. | ECCE | 2,293 |
| 8. | ECCE +PC IOL | 1,672 |
| 9. | Evisceration | 901 |
| 10. | Glaucoma operation | 1,756 |
| 11. | ICCE | 2,293 |
| 12. | ICCE + AC IOL | 1,878 |
| 13. | Inoculation | 889 |
| 14. | Lid repair | 913 |
| 15. | Lid tumor excision | 1820 |
| 16. | Probing | 6831 |
| 17. | Pterrigium removal | 1,042 |
| 18. | Scleral operation | 1,756 |
| 19. | Scleral Operation | 1,753 |
| 20. | Scleral tear | 1,581 |
| 21. | Skin Graft Release of Scar | 1,820 |
| 22. | Strabotomy/squint | 1,893 |
| 23. | Sub-conjunctiva injection | 694 |
| 24. | Tarsal picking/bilateral | 721 |
| 25. | Tarsotomy | 1,047 |

## 6. Dental Procedures

| | | |
|---|---|---|
| 1. | Abscess tooth drainage | 312 |
| 2. | Alveolar bone fracture/splitting | 1,102 |
| 3. | Amalgam filing | 467 |
| 4. | Composite resin filling | 779 |
| 5. | Excision of periodontitis | 767 |
| 6. | Preapicalaspextomy | 775 |
| 7. | Root canal filling | 761 |
| 8. | Splinting | 807 |
| 9. | Supra & sub gingival(calculus scaling) | 757 |
| 10. | Surgical extraction | 760 |
| 11. | Temporary filling | 856 |
| 12. | Tooth extraction | 463 |
| 13. | Ultrasonic scaling | 775 |
| 14. | With arch bar & wire | 1,113 |

## 7. Radiology Test

**ማስሰቢያ፡** –ተገልጋዩ በቀጥታ ከሚከፍላው የግል ህክምና አገልግሎት ክፍያ (PW price) ላይ የአላቂ እቃዎች ዋጋ (PW supply cost) ተቀንሶ ለሆስፒታሉ ገቢ ከተደረገ በኋላ ቀሪው በግል ህክምና አገልግሎት የተገኘ ትርፍ ይሆናል፡፡

| No | Services | PW Price | PW Supply cost |
|---|---|---|---|
| 1. | Abdomen/Plain/adult | 60 | 20 |
| 2. | Abdomen/Plain/Infant | 50 | 10 |
| 3. | Barium Enema | 81 | 27 |
| 4. | Barium Meal Follow through | 232 | 57 |
| 5. | Ba-Swallow | 93 | 31 |
| 6. | Ba-Swallow with caster oil | 172 | 36 |
| 7. | Cervical Myelograph | 141 | 40 |
| 8. | Cervical spine PA & LAT | 120 | 40 |
| 9. | Chest/adult/PA | 60 | 20 |
| 10. | Chest/adult/PA & LAT | 120 | 40 |
| 11. | Chest/infant/AP | 50 | 10 |
| 12. | Chest/infant/PA & LAT | 100 | 25 |
| 13. | Cyst Uretrography | 174 | 38 |
| 14. | Dental X-ray | 100 | 40 |
| 15. | ECG | 70 | 30 |
| 16. | Fistulography | 121 | 40 |
| 17. | Foot | 60 | 20 |
| 18. | Forarm/Adult | 60 | 20 |
| 19. | Forarm/Infant | 40 | 10 |
| 20. | Fumer/adult | 60 | 20 |
| 21. | Fumer/Infant | 40 | 10 |
| 22. | GVU/IVP | 227 | 73 |
| 23. | Hand | 60 | 20 |
| 24. | Histography | 184 | 66 |
| 25. | Humorous | 60 | 20 |
| 26. | Joint Ankle | 60 | 20 |
| 27. | Joint Cervical | 60 | 20 |
| 28. | Joint Elbow | 60 | 20 |

| No | Services | PW Price | PW Supply cost |
|---|---|---|---|
| 29. | Joint Hip | 60 | 20 |
| 30. | Joint Knee | 60 | 20 |
| 31. | Joint Shoulder | 60 | 20 |
| 32. | Joint Wrist | 60 | 20 |
| 33. | Leg/ Infant | 50 | 10 |
| 34. | Leg/Adult | 60 | 20 |
| 35. | Lumbar Spine/Infant | 100 | 20 |
| 36. | Lumbar Spine/PA & LAT | 120 | 40 |
| 37. | Lumbar-Lumbar/Adult | 60 | 20 |
| 38. | Lumbo- Sacral/Adult | 120 | 40 |
| 39. | Mandible PA & LAT | 120 | 40 |
| 40. | Nasal bone | 60 | 20 |
| 41. | Pelvis/Adult | 60 | 20 |
| 42. | Pelvis/Infant | 50 | 10 |
| 43. | Sinus PA | 60 | 20 |
| 44. | Skull PA & LAT | 120 | 40 |
| 45. | Thoraco Spine PA & LAT | 120 | 40 |
| 46. | Thoraco Spine PA and LAT/ adult | 120 | 40 |
| 47. | Thoraco Spine PA and LAT/ child | 100 | 20 |
| 48. | Ultrasound | 90 | 20 |
| 49. | Fluoroscopy Exam | 350 | 50 |
| 50. | Electroencephalography (EEG) | 300 | 100 |
| 51. | CT | 400 | 200 |
| 52. | MRI | 500 | 250 |

## 8. ENT

| | | |
|---|---|---|
| 1. | tympanoplasty - | 3780 |
| 2. | cortical mastoidectomy<br>- | 3990 |
| 3. | radical mastoidectomy | 3967 |
| 4. | meatoplasty | 2001 |
| 5. | correction of deformed ear | 2001 |
| 6. | preauricular sinus exploration and excision | 1923 |
| 7. | keloid excision from one ear | 850 |
| 8. | nasal polypectomy from ne nose | 1757 |
| 9. | septoplasty | 2229 |
| 10. | rhinoplasty | 3251 |
| 11. | antrochoanal polypectomy | 2463 |
| 12. | nasal bone fracture reduction | 1175 |
| 13. | septal wall abscess drainage | 650 |

## 9. Miscellaneous

| No. | Services | PW price | PW Supply cost |
|---|---|---|---|
| 1. | Card/ outpatient Consultation Fee for Gps | 45 | 5 |
| 2. | Card/ outpatient Consultation Fee specialist | 60 | 5 |
| 3. | Inpatient senior Consultation per day | 50 | |
| 4. | IPD, Bed Day according to the class level | 100-120 | |
| 5. | Medical examinations Certificate | 45 | 5 |
| 6. | Physician Round per day per patient | 10 | |
| 7. | Physiotherapy procedures according to the level of intervention | 25-40 | |
| 8. | Nerve conduction study | 350 | 100 |
| 9. | Anesthetics procedure | 500 | 50 |

**የግል ህክምና አገልግሎት የትርፍ ክፍፍል**

ከተጣራው የግል ህክምና ገቢ 70% ለጤና ባለሙያ 15% ለሆስፒታል እና ቀሪው 15% ለአስተዳደርና ለድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ይውላል፡፡ ከሁሉም እኩል 1 አንድ በመቶ ተቀንሶ 3 በመቶ የግል ህክምና ክፍል ቀጣይነትን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ በዚህም መሰረት የጤና ባለሙያው ድርሻ የሆነው 69 በመቶ ሰንጠረዥ /ሀ/ ላይ በተመለከተው መሰረት ለአስተዳደር ሰራተኞች ድርሻ 14 በመቶ በሰንጠረዥ /ለ/ ላይ በተመለከተው መሰረት የቁርጥ ክፍያ ተከፋዮች ድርሻ ከተቀነሰ በኋላ ቀሪው ወደ 100% ተቀይሮ የሚከፋፈል ይሆናል፡፡

**ሰንጠረዥ ሀ**

| Sources of revanue | | | Specialist | GP | OPD Nurse | Lab. Professional | Radiographer | Radiologist | Biomed | Anesthetist | Anesthesiologist | OR & recovery Nurse | Assistant | Ward Nurse | Pool |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **Consultation (Card)** | | | 75% | | 25% | | | | | | | | | | |
| | | | | 75% | 25% | | | | | | | | | | |
| **Laboratory** | | | | | | 50% | | | 5% | | | | | | 45% |
| **U/ saund** | | | | | | | 15% | 75% | 10% | | | | | | |
| **x-ray** | | | 15%* | | | | 55% | 25% | 5% | | | | | | |
| **Operation** | | | 70% | | | | | | 2% | | | 13% | 10% | 5% | |
| **Nursing procedure** | | | 20%* | | | | | | | | | | | 70% | 10% |
| **In patient** | | | 40% | 30% | | | | | | | | | | 20% | 10% |
| **EKG** | | | 40%* | | 50% | | | | 10% | | | | | | |
| **Indoscopy** | | | 70%* | | 25% | | | | 5% | | | | | | |
| **Anesthesia** | | | | | | | | | 2% | 78% | 20% | | | | |
| **Pool** | 70% | 70% medical/ internal Med./ & GP** | | | | | | | | | | | | | |
| | | 30 % OBY/ GYN & Surgen | | | | | | | | | | | | | |
| | 20% | Nurse | | | | | | | | | | | | | |
| | 10% | Pharmacy | | | | | | | | | | | | | |

*ና** በስፔሻሊስት ሃኪምና ወይም/ና በጠቅላላ ሃኪም የተገኘውና በስራው የተሳተፈው ሃኪም የተጠቀሰዉን ድርሻ ያገኛል፤ ሁለቱም በሚሳተፉበት ግዜ በስራ ጫናቸው መጠን ይካፈላሉ

| | |
|---|---|
| **Administrative staff** | |
| Accountant | 17.7% |
| Cash collectors | 15.9% |
| Store man | 2.1% |
| Main casher | 2.1% |
| Cleaner | 7.5% |
| Porter | 3.3% |
| Laundry | 5.7% |
| Lab assistant | 1.4% |
| X-ray assistants | 1.4% |
| Operator | 1.4% |
| CSSD | 3.6% |
| Registration | 12.9% |
| Guard | 3.3% |
| Miscellaneous * | 21.3% |
| **Department Heads** | ብር |
| **CEO/Provost** | እስከ 3000 |
| **Medical Director/ Vice Provost /Vice CEO** | እስከ 2500 |
| **Private wing coordinator** | እስከ 4000 |
| Finance Head | እስከ 1000 |
| Audit Head | እስከ 600 |
| Registration(MR) Head | እስከ 300 |
| Cleaner's Head | እስከ 300 |
| Gard/Security Head | እስከ 300 |
| Driver's head | እስከ 300 |